EFDA
የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ETHIOPIAN FOOD & DRUG AUTHORITY

ከኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# «ከተሞችን ከትምባሆ ጭስ ነፃ ለማድረግ ቅንጅታዊ አሠራር በመተግበር ውጤት መመልከት ተችሏል»

**የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ሄራን ገርባ**

ትምባሆ አጫሽነት ወይም ተጠቃሚነት በዓለም ላይ በየዓመቱ ከ8 ሚሊዮን በላይ ሰዎችን ለሞት ከሚዳርጉ ትልልቅ የሕዝብ ጤና ችግሮች ውስጥ አንዱ ነው። መረጃዎች እንደሚያመላክቱት በትምባሆ ጭስ ተጠቃሚነት ምክንያት ከሚሞቱት ሰዎች ውስጥ ከ 7 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑት በቀጥታ ትምባሆን የሚያጨሱ ሲሆኑ ከ 1 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑት ደግሞ ለጭሱ በተለያየ መንገድ የሚጋለጡ ናቸው።

በማንኛውም መንገድ ትምባሆን ማጨስና በየትኛውም ደረጃ ለትምባሆ ጭስ መጋለጥም ሆነ ማጨስ አደጋው አስከፊ ነው፡፡ በኢትዮጵያም ይህን ታሳቢ በማድረግ ከተሞችን ከትምባሆ ጭስ ለመከላከል የተለያዩ ተግባራት በመከናወን ላይ ናቸው፡፡

በባለፈው ሁለት ተከታታይ እትማችን አዲስ አበባ ከተማን ከትምባሆ ጭስ ነፃ ለማድረግ ተጀመረውን ኢንሼቲቭ በሚመለከት ከኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ከወይዘሪት ሄራን ገርባ ጋር የተደረገ ቃለ-መጠይቅ ይዘን መቅረባችን ይታወሳል፡፡

በዛሬው እትማችንም ከኢንሼቲቩ የተገኙ ውጤቶችና ምርጥ ተሞክሮችን እንዲሁም በሕብረተሰብ ንቅናቄ እያንዳንዱ ዜጋ ትምባሆ እንዳይጭስበት መብቱን እንዲጠይቅ ማስገንዘብን በተመለከተ ላነሳንላቸው ጥያቄ በሠጡት ምላሽ ዋና ዳይሬክተራ እንደገለፁትም፣ በትምባሆ ቁጥጥር የዓለም አቀፍ ጤና ድርጅት በግለሰብና በተቋም ደረጃ በድምሩ አምስት ጊዜ ለኢትዮጵያ ዕውቅና ሰጥቷል።

ይህ ውጤት የመጣው በሥራ ነው፡፡ ድርጅቱ አፈፃጸሙን የሚከታተልበት የራሱ የሆነ አሠራር አለው። በዓለም አቀፍ ደረጃ በየዓመቱ ትምባሆን የሚመለከቱ የሚወጡ ሪፖርቶችም አሉ። በተለይ እ.ኤ.አ በ2021ዱ ሪፖርት ኢትዮጵያ በብዙ ነገር ለውጥ እያመጣች እንደሆነ አሳይቷል፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ ጠንካራ ሕግ እንዳለን



ይታወቃል። ጠንካራውን ሕግ በማስከበር ረገድም ለሌሎች ሀገራት ምሳሌ መሆን መቻል አለብን። ሕጉን በአግባቡ አስተግብሮ በመቀጠል ረገድ ሥራዎች መሠራት አለባቸው። ገበያ ላይ ያለው ትምባሆ የጤና ማስጠንቀቂያው ሕጉ በሚያስቀምጠው አግባብ ነው ወይ? መቶ በመቶ ከትምባሆ ጭስ ነፃ መሆን ያለባቸው አካባቢዎች በእርግጥስ መቶ በመቶ ነፃ ናቸው ውይ? የሚለው በደንብ እየታየ መሄድ አለበት፡፡

የትምባሆ ቁጥጥር በርካታ ባለድርሻ አካላትን ያሳትፋል። ጠንካራ የትብብር ማዕቀፍ ፈጥሮ ሥራን ከመሥራት አንፃር ሁሉም ተቋም የተሰጠው የየራሱ ኃላፊነት አለበት። ከአዲስ አበባ ትምባሆ ኢንሼቲቭ የተማርነው ነገር የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን አንድ አድርጎ ማምጣት ነው። ከትምባሆ ማጨስ ጋር ተያይዞ ሌሎችንም ባለቤት ተደርጎ የመሥራት ልምድ ነው፡፡

ለምሳሌ ሺሻ ሕገወጥ ነው፡፡ በእኛ ሀገር ሙሉ በሙሉ ክልከላ የተደረገበት ነው፡፡ በተፈጠረ ጥምረት ደንብ ማስከበርና የፖሊስ አካላት ብዙ የሺሻ የሚጨስባቸው ተቋማትን ሺሻ የሚጨስባቸውን ዕቃዎች በጣም በከፍተኛ ሁኔታ እየያዙ መሆናቸውን እየተመለከትን ነው።

ከተሞችን ከትምባሆ ጭስ ነፃ ለማድረግ ቅንጅታዊ አሠራርን በመተግበር ውጤትን መመልከት ተችላል። በተፈጠረው የመተባበርና የጋራ አድርጎ የመሥራት ስሜትና ውጤት ላይ ከፍተኛ ልምድ ማግኘት ችለናል። ይህን ተሞክሮ ሌሎች ክልሎችም ጋር መስፋት ያለበት ነው።

የአመራሩ ተሳትፎና ቁርጠኛ መሆንም ሌላ ሊነሳ የሚገባው ልምድ ነው፡፡ በተለይ ከላይ እስከ ታች ያለው የአዲስ አበባ አስተዳደር አመራር ይሄን ጉዳይ በደንብ መያዙ ነው። አመራሩ በየጊዜው ይከታተለዋል፡፡ ቢሮ ላይ ተጠሪ ባለሙያዎችን በመመደብ ክፍለ ከተማን ይደግፋሉ። ክፍለከተማ ወረዳን ይደግፋል። በየጊዜውም ክትትል ይደረጋል፡፡ እኛም በፌዴራል ደረጃ በየጊዜው የሚሠራውን ስራ እናያለን። እንከታተላለን።

ከዚያ ውጭ ዘላቂታዊ መፍትሔ የሚሆኑትን በማህበረሰብ ንቅናቄ መደገፉ፣ ሕብረተሰቡን ከማስተማር አንፃር እንዲሁም የግሉን ዘርፍ በተለይ ነጥሎ በማውጣት ሁሉም የችግሩ ተባባሪ አድርጎ ፈርጆ ከመቀጠል ይልቅ በቡና በምግብ ቤቶች ዙሪያ ለሚሠሩ የድርጅቶቹ ሥራ አስኪያጆች ሥልጠና መስጠትና ለቁጥጥሩ ተባባሪ እንዲሆኑ የማግባባት ሥራ መሠራቱ ወሳኝ ልምድ ውጤት የተገኘበት ነበር።

እንደ ዋና ዳይሬክተሯ ገለፃ፣ በተካሄዱ የንቅናቄ መድረኮች ሕብረተሰቡ ካወቀ ተባባሪ አጋዥና ባለቤት እንደሚሆን አይተናል። ለአብነትም ችግር ያለባቸው ምርቶች ሪፖርት አድርጎ ርምጃ የተወሰደባቸው ሁኔታዎች አሉ። ህብረተሰቡን የቁጥጥር አካል በማድረግ ሂደት ሕጋዊና ሕገወጡን እንዴት መለየት እንችላለን የሚል ጥያቄም ይነሳል። በዚህ ረገድ በመድኃኒት ብዙ ሥራ ሠርተናል፡፡ ሌሎቹም ላይ በደንብ መሥራት አለብን። ስለዚህ ሕብረተሰቡ ምን አይቶ እንደሚገዛ፣ ምን አይቶ እንደሚጠቀም ማወቅ አለበት። ይህ ካልሆነ ለብዙ የጤና ችግሮች ይጋለጣል፡፡

ንቅናቄው የተፈጠረውም ይህን ታሳቢ በማድረግ ነው። ንቅናቄው የተፈለገውን ለውጥ እንዲያመጣም ለአንድ ሰሞን ድንኳን ተጠሎ የሚደረገው ብቻ ሳይሆን ተከታታይ ሥራ መሥራት አለበት። የሚዲያ አካላት ለዚህ በጣም አጋዥ መሆን አለባቸው።

የግንዛቤ ፈጠራን በተመለከተ ለአብነት የአዲስ አበባ ምግብ፣ መድኃኒት፣ ጤናና ጤና ነክ ግብዓቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ጥሩ ተሞክሮን አስመልክቷል። ይህም ትምህርት ቤቶችን መጠቀም ነው። ተማሪዎች ሲገቡ መዝሙር በሚዘምሩበትና ሰንደቅ ዓላማ በሚሰቀልበት ሰዓት የተለያዩ ትምህርቶችን ማለት ትምባሆና አደገኛ እጾች ማጨስ በጤና ላይ ስለሚያስከትለው ጉዳት እዚያው ላይ ያለምንም ወጪ ማስተማር ነው፡፡

መሰል ቀጣይነት ያላቸው ሥራዎች በትምህርት ቤቶች ሚኒሚዲያ ተጠቅሞ መሥራት፣ ማህበራዊ ሚዲያን መጠቀም የግድ ይላል፡፡ ጉዳዩ ማህበራዊ ጉዳይ ስለሆነ መገናኛ ብዙሃን በጣም በቅናሽ በሆነ ዋጋ ካልሆነም ደግሞ በነፃ ሊሠሩ መልክቶችን ሊያስተላፉ ይገባል።

የሕዝብ ንቅናቄው በተደረገ ሰሞን የምናያቸው ብዙ ለውጦች አሉ። ስለዚህ የነፃ የስልክ መስመርም አዘጋጅቶ እሱን በደንብ እያስተዋወቁ ያንን ሕብረተሰቡ አስተያየት የሚሰጥበት ጥቆማ የሚሰጥበት ካደረግን ባለቤት እየሆነና የሚፈለገው ለውጥ እየመጣ ይሄዳል።

Tel : +251-11-552-41-22
+251-11-552-41-22
P.o.box. 5681
Free call. 8482

http://www.fmhaca.gov.et/contact/
E-mail contactefda@efda.gov.et
Telegram channel link
https://t.me/ethiopianfoodanddrugauthority/

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ